ከመጽሐፍት ዓለም

## ኦሪት ዘፍጥረት

በዛሬ የመጽሐፍት ዓለም ፕሮግራማችን ከስምንቱ ብሔረ ኦሪት ወይም ከአምስቱ የሙሴ መጻሕፍት የመጀመሪያ የሆነውን ኦሪት ዘፍጥረትን የሚመለከቱ ጥናታዊ ጹሑፎችን አቀናጅተን ይዘንላችሁ ቀርበናል።

1. ኦሪት ዘፍጥረት - ስያሜው «በረሺት» ትርጉሙም «መጀመሪያ» ማለት ነው። «በዕብራይስጡ መጽሐፍ ቅዱስ ምዕራፍ 1፥1 ላይ ያለው የመጀመሪያው ሐረግ «በረሺት» የሚል ሲሆን ትርጉሙም «መጀመሪያ» ማለት ነው። ምንያቱም ጥንታውያን ጹሑፎች ስያሜያቸውን የሚያገኙት በጹሑፉ መጀመሪያ ላይ በሚገኙት ቃላት ነበር። «ጀነሲስ» የሚለው የእንግሊዝኛ ስያሜ የተቀዳው የ70 ሊቃናት የግሪክ ትርጉም በዘፍ 2፥4 እና 5፥1 ላይ «ጄነሲስ» ካለው ቃል ነው። «ኦሪት ዘፍጥረት» የሚለው «የአማርኛ» ስም ከዕብራይስጡና ከግሪኩ ጋር ተመሳሳይ ትርጉም አለው። «ኦሪት» ማለት ሕግ፣ ፍትሕ፣ ፍጡርነት፣ ጥንት፣ ዘር፣ ሥር፣ ምንጭ፣ ልደት ትውልድ ማለት ነው። «ፍጥረት» ከሚለው ቃል ፊት የሚገኘው «ዘ» የግዕዝ ዘርፍ አያያዥ መስተዋድድ ሲሆን የአማርኛ አቻው «የ» ነው። ስለዚህ «ኦሪት ዘፍጥረት» ማለት የፍጥረት ሕግ፣ የአፈጣጠር ደንብ፣ የፍጥረት ሥር፣ ምንጭ፣ ልደት፣ የፍጥረት ትውልድ ማለት ነው። በግዕዝ ኦሪት ዘልደት መባሉ ፍጥረተ ዓለምንና ልደተ አበውን የሚናገር በመሆኑ ነው»«ጀነሲስ»በግዕዝ ኦሪት ዘልደት ማለት ነው፣ (ኢንተርናሽናል ባይብል ሶሳይቲ 2001. (1993 ዓ.ም))

## ኦሪት ብሂል

«ኦሪት» ብሂል፣ «ሕግ ትምህርት ማለት ነው። ቃሉ ኦራይታ ከሚለው የጥንት የሶርያ ቋንቋ የተገኘ ነው። በተለይም ኦሪት የመጽሐፍ ቅዱስ መጀመሪያ የሆኑትን አምስቱን መጻሕፍት ያመለክታል» (የመ. ቅ. መዝገበ ቃላት 1989)

«ኦሪት» ብሂል በአበው ትርጓሜ

«ኦሪት ዘልደት» ማለት« ዜና ፍጥረት» ማለት ነው።

«ኦሪት» ማለት ቃለ እግዚአብሔር ማለት ነው። «እግዚአብሔር ከመዝ በሎሙ» «እንዲህ በላቸው» እያለ ሠርቶአታልና።

«ኦሪት» ማለት «ቃል ቅዱስ ማለት ነው።» «ወወረደ ኤር ቅዱስ» እንዲል።

«ኦሪት» ማለት «የተላከ ብርሃን ማለት ነው።» ሕጉ ብርሃን ነውና።

«ኦሪት» ማለት «መጽሔት ማለት ነው።» የዓይንን ጉድፍ፣ የጥርስን ዕድፍ መስታውት ለይቶ እንዲያሳይ ጽድቅና ሐጢአትን ቆጥራ፣ ቆጥራ አሳይታለችና።

«ኦሪት» ማለት «ምሥክር ማለት ነው።» «ስማዕ እስራኤል አሐዱ ውእቱ እግዚአብሔር አምላክከ» ብላ አምልኮቱን ትመሰክራለችና። ዘዳ 6፥4

«ኦሪት» ማለት« ሕግ፣ ሥርዓት ማለት ነው።» ሕግ ሠርታ ሕግ ይሁናችሁ፣ ሥርዓት ሠርታ ሥርዓት ይሁናችሁ ብላ ታስተምራለችና በማለት አበው ኦሪትን በዓላማዋና በግብሯ ተርጉመዋታል። ይህ ትርጓሜ ግን የሚያገለግለው ለአምስቱ የሙሴ መጻሕፍት ሁሉ ነው እንጅ ለኦሪት ዘፍጥረት ብቻ አይደለም። «ኦሪት» የአምስቱ መጻሕፍት የጋራ ስም ነውና። ይህ ትርጎሜ የመጽሃፋን ይዘት የተከተለ ነው።

## ይዘታዊ ስያሜው

አምስቱ የሙሴ መጽሐፍ በግዕዝ አምስቱ ብሔረ ኦሪት ይባላል። በቅድሚያ ወደ ሀገራችን የገቡ እና በሀገራችን ቋንቋ በግዕዝ የተተረጎሙ የመጀመሪያዎቹ የኦሪት መጻሕፍት እንደሆኑ ይነገራል። እስከዛሬም ድረስ በትልልቅ አድባራት በአንድ ላይ ተጽፈው እንደ አራቱ ወንጌል አምስቱ ብሔረ ኦረት ይገኛሉ። «ብሔረ ኦሪት ማለትም አንቀጸ ኦሪት፣ ሕገ ኦሪት ማለት ነው።» አምስቱ ብሔረ ኦሪት ከኦሪት ዘልደት (ዘፍጥረት) እስከ ዘዳግም ያሉት መጻሕፍት ናቸው።

**ስምንቱ ብሔረ ኦሪት** - አምስቱ ብሔረ ኦሪት በማለት ፈንታ «ስምንቱ ብሔረ ኦሪት» በመባል በቤተክርስቲያናችን ይጠራሉ። ስያሜው የተወሰደው ከሰባ ሊቃናት ነው። ይኸውም ሦስቱን የኦሪት ተከታይ የታሪክ መጻሕፍት ማለትም ኢያሱን፣ መሳፍንትን እና ሩትን በአምስቱ የሙሴ መጻሕፍት ላይ በመደመር ነው። ከዚህ የተነሳ ስምንቱ ብሔረ ኦሪት ሲባል ከኦሪት ዘልደት እስከ መጽሐፈ ሩት ድረስ ያሉት ናቸው። ነገር ግን ኢያሱ፣ መሳፍንት፣ ሩት የታሪክ መጻሕፍት እንጅ የህግ መጻሕፍት አይደሉም።

**ፔንታቱክ** - እነዚህ አምስቱ የኦሪት መጻሕፍት በግሪክ ፔንታቱክ (አምስቱ የሙሴ የሕግ መጻሕፍት) ተብለው ይጠራሉ። በዕብራይስጥ ቶራ (ሕግ) ተብለው ይጠራሉ። ከዚህ በላይ ያየነው ጠቅላላ ስለ አምስቱ መጻሕፈተ ኦሪት የተሰጠውን የጋራ ስያሜ ነው።

2. ጸሐፊው - ጸሐፊው ነቢዩ ሙሴ ነው። ኦሪት ዘፍጥረት ትምህርቱ ታሪኩ በጠቅላላ ቅድመ ሙሴ የነበረውን የእግዚአብሔርን ሥራና ፍጥረት፣ የአበውን ታሪክ (ዜና አርስተ አበውን) የያዘ ሲሆን በመንፈስ ቅዱስ ገላጭነት ቀድሞ ይነገር የነበረውን ሁሉ በዘመኑም የነበረውን አሰባስቦ አቀናጅቶ ጽፎታል። ለዚህም ቤተ አይሁድና ቤተ ክርስቲያን እንዲሁም ራሱ መጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ምስክሮች ናቸው። ስለዚህም መተርጉማን አበው እንዲህ ይላሉ። «በደብረ ሲና የተነገረውን ጌታ ጻፈው ብሎት አምስት ክፍል አድርጎ ጽፎታል። እሊህም ኦሪት ዘልደት፣ ኦሪት ዘጸአት፣ ኦሪት ዘሌዋውያን፣ ኦሪት ዘኁልቅ፣ ኦሪት ዘዳግም ናቸው» (ትርጓሜ ኦሪት)። የትርጓሜው መቅድምም እንዲህ ይላል- «መጀመሪያው መጻሕፍ ኦሪት ዘልደት (ዘፍጥረት) ግን የተነገረ ከዚያ በፊት ሲሆን የተጻፈውም እንደ ሌሎች መጻሕፍት በሙሴ እንደሆነ ከጥንት ጀምሮ ይታመናል» (መግለጫውን ተመልከት)።

የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ስለዚህ እንዲህ ይላል- «ሙሴ የሕግ (የትዕዛዛት) ክፍሎችን እንደጻፈ በኦረት ውስጥ ተነግራል። ዘጸ 24፥4፤ 34፥27፤ ዘዳ 31፥9-24። ከዚህም ጋር የእስራኤልን የጉዞ ታሪክ (ዘጸ 17፥14፤ ዘኍ 33፥2-49) መዝሙሩንም እንደጻፈ ተገልጧል። ዘዳ 31፥22፤ 32፥1-14። ከነዚህም ክፍሎች ሌላ ሙሴ ብዙዎችን ሳይጽፍ አልቀረም። ከሙሴ በፊት ስለነበሩ አባቶች ታሪክ አስቀድመው ሌሎች ጽፈው ይሆናል። እንዲህም ከሆነ ሙሴ ታሪካቸውን አንድ ላይ ሰብስቦ ሊጽፈው ይችላል። ሙሴ ስለራሱ ሞት (ዘዳ 34፥1-12)፣ ከሞተ በኋላ ስለሆኑት ድርጊቶች የጻፈ አይመስልም (ለምሳሌ ዘኁ 32፥34-42)። ከሙሴ በኋላ የነበሩ ጸሐፊዎች አልፎ አልፎ ማብራሪያ የሰጡ ይመስላል (ለምሳሌ ዘፍ 36፥31)። ምንም እንኳ ረቂቁን የገለበጡት አንዳንድ ማብራሪያ ቢጨምሩም አንዳንድ ቃላትንም በዘመናቸው ወደሚነገረው ዕብራይስጥ ቢለውጡ ጠቅላላ

ው ሕግ ከሙሴ እንደተገኘ ይታመናል። ዮሐ 1፥17። ጌታችን ኢየሱስና ሐዋርያት እን ደ አይሁድ መምህራን ሁሉ ኦሪት በሙሴ መጻፉን እንዳረጋገጡ ግልጽ ነው። ማቴ 8፥ 4፤ ማር 12፥26፤ ሉቃ 24፥44፤ ዮሐ 7፥19፤ የሐዋ ሥራ 28፥23፤ 1ቆሮ 9፥9፤ ዕብ 9፥19 -20» (ዝኒ ከማሁ 1989)

<u>መቼ ተጻፈ</u> ?

ትርጓሜ ኦሪት መግቢያ ላይ የተሰጠው ጊዜ ኦሪት ዘፍጥረትን ባያካትትም የሙሴን የጹ ሑፍ ዘመን ስለሚያካትት ነባሩንም ታሪክ ሙሴ አቀናጅቶ መጻፉ ስለታመነ በ1ሺህ 500 ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ገደማ እስራኤል በግብጽ ከወጡበት ጊዜ ጀምሮ ሙሴ እስካረ ፈበት ጊዜ ድረስ ባለው ዘመን ተጽፎአል። እንደ ዓለም አቀፉ የመጽሐፍ ቅዱስ ማሕ በር ማብራሪያ ደግሞ «ሙሴ የነበረበት ትክክለኛ ዘመን ብዙ በማያሻማ እርግጠኛነት በ 1ኛ ነገሥት ውስጥ ተገልጦአል። የሰሎሞን ንግሥና አራተኛ ዓመት እስራኤላውያን ከግ ብጽ የወጡበት 480ኛ ዓመት መሆኑ ተጠቅሶአል። 1ኛ ነገ 6፥1። ይህም ከ1446-966 ዓ. ቅ.ክ. መሆኑ ነው። ከ1446-1406 ዓ.ቅ.ክ. ድረስ እስራኤል በምድረ በዳ ባሳለፉት ዓመታ ት ሙሴ «ፔንታቱክ» ተብለው የሚታወቁትን አምስቱን የኦሪት መጻሕፍት እንደጻፈ ይ ገመታል» ኢንተርናሽናል ባይብል ሶሳይቲ 2001.ገጽ 1

<u>በምን ቋንቋ ተጻፈ?</u>

መጀመሪያ በዕብራይስጥ ተጽፎአል። በኋላ የታወቀው የትርጓሜ ሥራ በ70 ሊቃናት ወ ደ ጽርዕ (ግሪክኛ) መተርጎሙ ነው። ከዚያ በኋላ በብዙ ሺህ ቋንቋዎች ተተርጉሞ ለዓለ ም ሕዝብ በመዳረስ ላይ ነው።

<u>ወደ ግዕዝስ መቼ ተተረጎመ?</u>

ሁለት ዓይነት አስተያየት አለ። አንደኛው በንግሥተ ሳባ ዘመን ከሰሎሞን ጉብኝት እን ደተመለሰች ነው የሚል ሲሆን። ሁለተኛው ደግሞ በአባ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን ከ330-360 ዓ. ም ባለው ክፍለ ዘመን ነው የሚል ነው። የመጀመሪያው አስተያየት ማረጋገጫ አ ልተገኘለትም። ምክንያት አንድም ኮፒ በዚያ ዘመን የተጻፈ ባለመገኘቱ፣ ሁለት የግዕዝ ቋንቋ ከአባ ሰላማ በፊት የነበረው መልክ አሁን ካለው ፍጹም የተለየ በመሆኑና በዚያ ም የጹሑፍ ሥርዓት የተሠራ መረጃ እስካሁን ባለመገኘቱ ነው። ሌላው ደግሞ አሁን የምንጠቀምበት የግዕዝ መጽሐፍ ቅዱስ የሚዛመደው ከሰባ ሊቃናት ትርጉም ጋር እንጂ ከዕብራይስጡ ብሉይ ኪዳን ጋራ አለመሆኑን ሊቃውንት በጥናት በማሳየታቸው ነው።

<u>ወደ አማርኛ መቼ ተተረጎመ?</u>

ወደ አማርኛ በአባ አብርሃም (አባ ሮሜ) ተተርጉሞ በ1816 አራቱ ወንጌላት፣ በ1821 ሐ ዲስ ኪዳን፣ በ1832 ሙሉ መጽሐፍ ቅዱስ ታትሞአል። ወደ ትግርኛ በአለቃ ተወልደ መድህን ወደ ኦሮምኛ በአናሲሞስ ነሲቡ ተተርጎሞአል። (ዝኒ ከማሁ 1989) ከዚህ ሁ ሉ አስቀድሞ ግን በመተርጉማን አበው ከግዕዝ ወደ አማርኛ በድርብ ትርጓሜ ሙሉ መጽሐፍ ቅዱስ ተተርጉሞ ነበር።

<u>በምዕራፍና በቁጥር መቼ ተከፈለ?</u>

ከጥንት ጀምሮ ቀጆች መጻሕፍትን በክፍል በምዕራፍና በቁጥር ለይተዋል። ነገር ግን እ ንደገና በ1228 ዓ.ም በምዕራፍ፣ በ1551 ዓ.ም ምዕራፉ በቁጥር መጽሐፍ ቅዱስ ሲከፈል

የመጽሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያ መጽሐፍ የሆነው ኦሪት ዘፍጥረትም ከተከታዮቹ መጻሕ ፍት ጋራ አሁን በምናየው መልክ ተዘጋጅቶአል። (የመ. መዝገበ ቃላት 1989)

## አስተምህሮውና ኣላማው

አባቶቻችን በትርጓሜአቸው ጠቅላላ ስለ ኦሪት ሲናገሩ ዘጠኝ ዋና ዋና ነገሮች መካተታ ቸውን ይናገራሉ። እነርሱም «ሕግ፣ ስምዕ፣ ትዕዛዝ፣ አኮቴተ እግዚአብሔር፣ ነገራተ እግዚአብሔር፣ ተግሳጽ፣ ምዕዳን፣ ጥበብ ሥጋዊ፣ ጥበብ መንፈሳዊ ናቸው» «ስምዕ» ምስክርነት ማለት ሲሆን «እስራኤል ሆይ ስማ እግዚአብሔር አምላክህ አንድ ነው» ያለው ነው። «ትዕዛዝ» ይህን ሥሩ፣ ይህን አትሥሩ የሚለው ነው። «አኮቴተ እግዚአ ብሔር» የሚለው እነ ሙሴ፣ እነ ማርያም እንዳመሰገኑት ምስጋና ያለ ነው። «ነገራተ እግዚአብሔር» የሚለው እግዚአብሔር ሙሴን ተናገረው የሚለው ነው። «ተግሳጽ» ላላፈው እንዲህ ለምን አደረግህ ብሎ መቅጣት ነው። «ምዕዳን» ለሚመጣው እንዲህ «አታድርግ» ብሎ መምከር ነው። «ጥበብ ሥጋዊ» የሥራን ቅዱስነት ማስተማር ነ ው። «ጥበብ መንፈሳዊ» በሃይማኖት ጸንታችሁ ጸልዩ፣ ጹሙ፣ በጎ አድራጊዎች ሁኑ ብላ ስለምታስተምር ነው።

**አከፋፈል**

ኦሪት ዘፍጥረት ብዙ ዓይነት አከፋፈል ያለው፣ ብዙ ትምህርትም የያዘ ፣ ልዩ የሥነ ጹሑፍ ባሕርይ የታየበት፣ ዜና አበውን በልዩ መንገድ የገለጠ መጽሐፍ ሲሆን አሁን ካ ለን የጊዜ እጥረት አንጻር አንዱንና በጣም አጭሩን አከፋፈል እንመለከታለን።

1. የዚህ ዓለም የመጀመሪያ ነገሮች የተገለጡበት ክፍል፣ ፍጥረት፣ የሰው ውድቀት፣ የጥፋት ውሃ፣ የባቢሎን ግንብ፣ ዘፍ 1-11።
2. የአባቶች ታሪክ። አብርሃም፣ ይስሐቅ፣ ያዕቆብ፣ ዮሴፍ፤ ዘፍ 12-50።
   (መጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት 1989)

**ማጠቃለያ-** ኦሪት ዘፍጥረት የመጽሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያ መጽሐፍ እንደመሆኑ ለሌሎ ች መጻሕፍት ሁሉ መነሻና መሠረት ነው። በእግዚአብሔርና በተፈጥሮ፣ በእግዚአብሔ ርና በሰው፣ በሰዎችና በሰዎች መካከል ያለውን ሕብረት አጉልቶ ያሳያል። መጽሐፉ አ ንድ አምላክ ብቻ ፈጣሪ፣ ገባሪ፣ ሁሉን ቻይ ዓለምን ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቶ የፈጠረ ሰውንም የፍጥረት ሁሉ ራስ፣ አዛዥ እና ናዛዥ አድርጎ ፈጥሮ ያስቀመጠ መ ሆኑን ያስተምራል። በኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 1 እና 2 ይህ የምንኖርበት ዓለምና በው ስጡ የሚካሄደው ማሕበራዊ ሕይወት እንዴት እንደጀመረ ስናነብ በኦሪት ዘፍጥረት ም ዕራፍ 3 የሰው ልጆች ማሕበራዊ ሕይወትና ሰላማዊ ሕይወት እንዴት እንደተዛባ እናነባ ለን። በምዕራፍ 4 በወንድማማቾች መካከል የተፈጠረውን የጦርነት ታሪክ መነሻ ስናነብ በምእራፍ 5 ሁለቱን ታላላቅ ትውልዶች እናያለን። እነርሱም የእግዚአብሔር ልጆችና የሰው ልጆች የተባሉት ናቸው። የሰው ልጆች የተባሉት በዓለም የተማረኩትን፣ ለፈቃደ ዓለም የተገዙትን እና የሚገዙትን የሰው ልጆች ሲያመለክት የእግዚአብሔር ል ጆች የተባሉት ደግሞ መንፈሳዊውንና የዳነውን የእግዚአብሔር ሕዝብ የሚያመለክት ነ ው። ከምዕራፍ 6-10 በሰው ልጆች ሐጢአት ምክንያት የመጣውን ቅጣትና የእግዚአብ ሔር ልጆች ደግሞ እንዴት ከመዐቱ እንደተረፉ እንመለከታለን። በምዕራፍ 11 የመጀ

መሪያዎቹ የቴክኖሎጅ ሰዎች ለእግዚአብሔር ባለመገዛት ሥራቸው እንደተበላሸ ስናነብ በምዕራፍ 12 አማኙ የአብርሃም ቤተሰብ በእምነት አዲስ ሥራ፣ አዲስ ቤተሰብ መጀ መሩንና መመሥረቱን እናነባለን። ከምዕራፍ 12-50 በጠቅላላ ያለው አብርሃምን መነሻ በማድረግ የመጀመሪያዎቹ የእምነት አባቶች ዜና ነው። የአብርሃም እምነት፣ ለእግዚአ ብሔር ፍቅር ልጁን መስዋዕት አድርጎ ማቅረብ፣ የይስሐቅ ታዛዥነት፣ የያዕቆብ ስደት፣ የዮሴፍ በሃይማኖት መክበር፣ የእስራኤል ሕዝብ ከቤተሰብ ወደ ሕዝብነት መለወጥ የ መጽሐፉ ዋና የታሪክ ክፍሎች ናቸው። ኦሪት ዘፍጥረት የሐዲስ ኪዳን ተስፋ የተነገረበ ት፣ የሃይማኖት ብርሃን የበራበት፣ እኔ ማን ነኝ? ከየት መጣሁ? ማን ፈጠረኝ? ዓለም ምንድን ነው? የምናየው ነገር ሁሉ ከየት መጣ? በማን ተፈጠረ? መቼ ተፈጠረ? እንዴት ተፈጠረ? የሚሉትን እና መሰል ሕይዎታዊ ጥያቄዎችን ሁሉ የሚመልስ መጽሐፍ ነው ። በመሆኑም መጽሐፉ በሰፊው ሊጠና፣ ሊነበብ ይገባዋል።

በረከተ አብርሃም፣ ይስሐቅ ወያዕቆብ በእኛ ላይ ለዘላለሙ ይኑር።
ሁሉን ለፈጠረ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን።

አዘጋጅ መምህር ልዑለ ቃል አካሉ

ምንጭ

1. የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት
2. መጽሐፍ ቅዱስ አዲሱ መደበኛ ትርጉም ከማጥኛ ጹሑፍ ጋራ
3. ትርጓሜ ኦሪት
4. መጽሐፍ ቅዱሳችን በአባ መልከ ጼዴቅ ያልታተመ